የሰ/መ/ቁ. 63699

15/11/2003

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አፔኖ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት ጠበቃ አቶ በረከት ቡሽራ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጥሩነህ ይመር አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ተጠሪ ለሥር የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በተከሣሽ ድርጅት /በአሁኑ አመልካች ድርጅት/ በዘበኝነት ተቀጥሬ እየሠራሁ የቆየሁ ቢሆንም በህመም ምክንያት ሥራዬን ያቆምኩ ስለሆነ ተከሣሽ አንዳንድ ያልከፈላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሣሽ ድርጅት በበኩሉ በሰጠው መልስ ከሣሽ በድርጅቱ ከታህሣሥ ወር 2001 እስከ ጥቅምት 2002 ለአሥራ አንድ ወራት በጥበቃ ሥራ ከቆዩ በኋላ በራሣቸው ፈቃድ ከተከሣሽ ድርጅት የተሰናበቱ ሲሆን በሰጡት አገልግሎት መሠረት የስንብት ክፍያ የተከፈላቸው በመሆኑ ሌሎች የሚከፈላቸው ክፍያዎች የሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቱም በሰጠው ፍርድ ተከሣሽ የስንብት ክፍያ ለከሣሽ መክፈሉን በማረጋገጥ ሌሎች ክፍያዎችን በሚመለከት ግን ከሣሽ በግልጽና በዝርዝር ያልጠየቁና በማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ በመሆናቸው ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ፍ/ቤት በበኩሉ በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ባይ በመልስ ሰጪ ድርጅት ለአንድ ዓመት የሠሩ መሆናቸው ስለተረጋገጠ መከፈል ያለባቸው ክፍያዎች ማለትም የትርፍ ሰዓት ክፍያ የዓመት ዕረፍትና የበዓላት ቀን ክፍያ የተከፈላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ መልስ ሰጪ ሊከፍላቸው ይገባል ብሏል፡፡

በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያለው ያሁን አመልካችም ለዚህ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ በደፈናው አንዳንድ ያልተከፈሉኝ ጥቅማ ጥቅሞችን አመልካች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለታቸው ብቻ የትርፍ ሰዓት የዓመት ዕረፍት እና የበዓላት ቀን ክፍያ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ስለ ክስ አቀራረብ

የተደነገጉትን መርሆዎችንና ስለማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትን መሠረት ያላደረገ ስለሆነ ውሣኔው ሊሻር ይገባል ብሏል፡፡

ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ መልስ ለመስጠት ባለመፈለጋቸው መብታቸው የታለፈ ሲሆን እኛም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ለተጠሪው የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ እንዲሁም የዓመት ዕረፍትና የበዓላት ቀናት የሠሩባቸው ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥራ ክርክር የፍትሐብሔር ባሕሪ ስላለው ክርክሩ መመራት ያለበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222 በክስ ጽሑፍ ላይ ስለሚሠፍሩ ነገሮች የተደነገገ ሲሆን በዚሁ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር /1/ በፊደል /ረ/ አንድ ክስ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች መያዝ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ከዚህ ሌላም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 80/1/ እንደተጠቀሰው ከሣሽ የሚጠይቀውን ሁሉ ዘርዝሮ በክሱ ወይም በአቤቱታው ማቅረብ እንደሚኖርበት በማያሻማ ሁኔታ ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪው ያልተከፈሉኝን ክፍያዎች አመልካች ይክፈሉኝ ከሚል ውጪ መክፈል ያለበትን ክፍያዎች በሕጉ መሠረት በዝርዝር ግለጽ አድርገው አላቀቡም፡፡ በግልጽ በዝርዝር ባልቀረበ ጉዳይ ደግሞ ሌላኛው ወገን እንዲከራከርበት ማድረግ የተጠቀሱትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥ/ሕ/ድንጋጌዎች መጣስ ይሆናል፡፡

ግለጽነት የጎደው ክስ ወይም አቤቱታ በቀረበ ጊዜ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 91/1/ እንደተጠቀሰው ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ከተከራካሪ ወገኖች በሚቀርበው ጥያቄ ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን ከተረዳ ክሱ ወይም አቤቱታው እንዲሻሻል ለማዘዝ ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ በያዝነው ጉዳይ በዚህ መልኩ ክሱ እንዲሻሻል አልተደረገም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ተጠሪው እንዲከፈላቸው የሚጠይቁት የዓመት ዕረፍት፣ የበዓላት ቀን እና የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች ለየትኛው ጊዜ እንደሆኑ ተለይተው ባልቀረቡበት እንዲሁም በእነዚህ ጊዜያት ተጠሪው የትርፍ ሰዓት ሥራ እና በበዓላት ቀናት የሠሩ ስለመሆናቸው፣ የዓመት ዕረፍት ያልተጠቀሙበት መኖር አለመኖሩ ማረጋገጫ ባለቀረበበት አመልካች እነዚሁኑ ክፍያዎች እንዲከፍሉ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ በፍትሐብሔር ሥ/ሥ ስለ ክስ አቀራረብ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ባልተከተለ ሁኔታ ከመሆኑም ሌላ ተጠሪው ክሱን በማስረጃ ሣያስረዱ የተወሰነ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የሥር የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 10/2/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03436 በቀን 28/10/2002 የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ የዓመት ዕረፍት፣ የበዓላት ቀናት፣ ትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎችን በገንዘብ ተለውጦ ሊከፍላቸው አይገባም ብለናል፡፡
4. አመልካች የዚህን ፍ/ቤት ወጪ የራሱን ይቻል፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ሃ/ዲ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት